**እ.ኤ.አ ኖቬምበር 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ አህፅሮት (Summary of NDVI analysis for 2nd dekade of November 2019)**

እ.ኤ.አ ኖቬምበር 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታን የሚያሳየዉ ከGEONETCast ኢንፍራስተራክቸር የሚገኘዉን የSPOT_VGT ግርድፍ የሳቴላይት መረጃን መቀበል ያለመቻላቸዉን ከNDRMC ICT ክፍል መረዳት ተችሏል።




**Vegetation Greenness (NDVI) in fraction for the second dekade of November 2019**

**Source: METEOSAT**

**Processed by LEAP (Version 3.1.1)**

| ካርታ 1 | ካርታ 2 |
|---|---|

የMETEOSAT መረጃን በመጠቀም በLivelihood Early Assessment Protection (LEAP) ሶፍትዌር የተተነተነው (ካርታ 2) እ.ኤ.አ የኖቬምበር 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ እንደሚያሳየዉ ለአለፉት ተከታታይ አሥር ቀናት በቤንሻንጉል ጉሙዝ በሁሉም ቦታ፣ በጋምቤላ ከምስራቃዊ ኪስ ቦታዎች በስተቀር በአብዛኛው፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ከሰሜናዊ ኪስ ቦታዎች በስተቀር በአብዛኛው፣ በሶማሌ ክልል ከሰሜናዊ ክፍል በስተቀር በአብዛኛው፣ በትግራይ ምዕራባዊ አጋማሽ በአብዛኛው እና ጥቂት የሰሜን ምስራቅ ክፍል፣ በአማራ ምዕራባዊ አጋማሽ በአብዛኛው እና ጥቂት ምስራቃዊ ክፍል፣ በኦሮሚያ ምዕራባዊ እና ደቡባዊ ክፍል በአብዛኛው እንዲሁም ጥቂት ምስራቃዊ እና መካከለኛው ክፍል በከፊል መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ሁኔታና በቀዳሚዎቹም ቀናት በነበረው እርጥበት ሣቢያ (ከብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የተገኘዉን ካርታ 5 እና 6 ይመልከቱ)፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ በአብዛኛው፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ከሰሜን ምስራቅ እና ደቡባዊ ጫፍ በስተቀር በአብዛኛው፣ በኦሮሚያ ምዕራባዊ ክፍል በአብዛኛው፣ ደቡባዊ ክፍል በከፊል፣ የተቀረው በተበታተነ መልኩ፣ በአማራ፣ በትግራይ፣ በሶማሌ፣ በሐረሪ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በተበታተነ መልኩ እንዲሁም በአፋር ደቡባዊ ክፍል ኪስ ቦታዎች ላይ የእፅዋት ሽፋኑ ከከፍተኛ እስከ መጠነኛ የመጨመር ሁኔታ የነበረዉ ሲሆን በመደበኛ ሁኔታ መኖር ከሚገባዉ የረዥም ጊዜ አማካይ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ደግሞ፣ በኦሮሚያ መካከለኛው፣ ሰሜናዊ እና ጥቂት ምስራቃዊ ክፍል በከፊል፣ የተቀረው በተበታተነ መልኩ፣ በአማራ ክልል መካከለኛው ክፍል በከፊል፣ የተቀረው በተበታተነ መልኩ፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ በተበታተነ መልኩ፣ በአፋር በተበታተነ መልኩ እንዲሁም በጋምቤላ፣ በሶማሌ እና በትግራይ ኪስ ቦታዎች ላይ የነበረዉ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ከመደበኛ በታች የነበረ ከመሆኑ በስተቀር በተቀሩት የአገሪቱ ክፍሎች ላይ በአብዛኛው መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ እንደነበር ምሥሉ ያመለክታል (ካርታ 4 ይመልከቱ)።




**Deviation NDVI in fraction for the second dekade of November 2019 (compared to the first dekade of November 2019), processed by LEAP (Version 3.0.4)**

ካርታ 3

እ.ኤ.አ የኖቬምበር 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ከኖቬምበር 2019 የመጀመሪያው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር የእፅዋት ሽፋኑ የመቀነስ ልዩነት ያሳየባቸዉ (በፍራክሽን ከ-0.30 እስከ -0.02) ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የም፣ አላባ እና ኮንታ ልዩ ዞኖች እንዲሁም ስልጤ፣ ጉራጌ፣ ሀድያ፣ ከምባታ፣ ከፋ፣ ዳውሮ፣ ሸካ እና ቤንችማጂ በአብዛኛው፣ ኮንሶ ልዩ ዞን፣ ጋሞጎፋ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ እና ደቡብ ኦሞ በተበታተነ መልኩ፣ የተቀሩት ዞኖች ኪስ ቦታዎቻቸው ላይ፣ ከሶማሌ ክልል ጅግጅጋ በአብዛኛው፣ የሊበን ሰሜናዊ ክፍል በከፊል፣ ሸንሌ፣ ፊቅ፣ ደገሃቡር እና አፍዴር በተበታተነ




**Vegetation Greenness (NDVI) in fraction for the second dekade of November 2019 [Compared to Normal], processed by LEAP (Version 3.0.4)**

ካርታ 4

እ.ኤ.አ የኖቬምበር 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ በመደበኛ ሁኔታ መኖር ከሚገባዉ የረዥም ጊዜ አማካይ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ከመደበኛዉ የመጨመር ሁኔታ (በፍራክሽን ከ0.03 እስከ 0.50) የታየባቸዉ አካባቢዎች ከአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር በከፊል፣ አገው፣ ሰሜን ሸዋ እና ምዕራብ ጎጃም በተበታተነ መልኩ፣ ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ጎንደር እና የኦሮሚያ ልዩ ዞን ኪስ ቦታዎች ላይ፣ ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ደቡብ ኦሞ በአብዛኛው፣ ኮንሶ ልዩ ዞን እና ቤንችማጂ በከፊል፣ ወላይታ፣ ጋሞጎፋ እንዲሁም ደራሼ እና አማሮ ልዩ ዞኖች በተበታተነ መልኩ፣ የተቀሩት ኪስ

መልኩ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ እና መዠንገር በአብዛኛው፣ ኑዌር በተበታተነ መልኩ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከማሺ በአብዛኛው፣ መተከል እና አሶሳ በተበታተነ መልኩ፣ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ሰሜን፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ፣ ሁሮጉድሩ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ቄለም ወለጋ እና ጅማ በአብዛኛው፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ቦረና፣ ጉጂ እና የባሌ ምዕራባዊ አጋማሽ በከፊል፣ በአማራ ክልል አገው በከፊል፣ የተቀሩት ዞኖች ላይ በአብዛኛው፣ በአፋር ክልል ዞን 3 በከፊል፣ የተቀሩት በተበታተነ መልኩ፣ በትግራይ ክልል በሁሉም ዞኖች ላይ በአብዛኛው እንዲሁም በሐረሪ ክልል እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በአብዛኛው እንደነበር ምስሉ ያመለክታል። በአንፃሩ የእፅዋት ሽፋኑ የመጨመር ልዩነት (በፍራክሽን ከ0.02 እስከ 0.30) ያሳየባቸዉ ከአፋር ክልል ዞን 1፣ 2 እና 4 በተበታተነ መልኩ፣ የተቀሩት ኪስ ቦታዎች ላይ፣ ከሶማሌ ክልል ጎዴ፣ ዋርዴር እና የአፍዴር ደቡባዊ ክፍል በአብዛኛው፣ ሊበን እና ቆራሄ በከፊል፣ ደገሃቡር፣ ፊቅ እና ሽንሌ በተበታተነ መልኩ፣ ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ደራሼ እና አማሮ ልዩ ዞኖች እንዲሁም ጌድዮ በአብዛኛው፣ ቡርጂ እና ኮንሶ ልዩ ዞኖች በከፊል፣ ጋሞጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቤንችማጂ እና ሲዳማ በተበታተነ መልኩ፣ ወላይታ፣ ባስኬቶ ልዩ ዞን እና ሸካ ኪስ ቦታዎች ላይ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ በከፊል፣ መተከል በተበታተነ መልኩ፣ ከማሺ ኪስ ቦታዎች ላይ፣ ከጋምቤላ ክልል በሁሉም ዞኖች ኪስ ቦታዎቻቸው ላይ፣ ከአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር እና አገው ኪስ ቦታዎች ላይ እንዱሁም ከኦሮሚያ ክልል የባሌ ምስራቃዊ ክፍል በከፊል፣ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ እና ምዕራብ አርሲ በተበታተነ መልኩ፣ ፣ምስራቅ ወለጋ፣ ጅማ እና ኢሉአባቦራ ኪስ ቦታዎች ላይ እንደነበር ምሥሉ ይጠቁማል። የተቀሩት ቤንሽንጉል ጉሙዝ በአብዛኛው፣ አፋር እና ሶማሌ በከፊል እንዲሁም ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ እና ጋምቤላ በተበታተነ መልኩ የነበረዉ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ከአለፈዉ የአስር ቀናት ጋር ተመሳሳይ እንደነበር ያሳያል። እ.ኤ.አ የኖቬምበር 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት ከአለፈዉ የአሥር ቀናት ጋር የነበረዉን የእፅዋት ሽፋን ልዩነት የሚያሳየው ምስል ያመለክታል (ካርታ 3 ይመልከቱ)።

ቦታዎቻቸው ላይ፣ ከአፋር ክልል ዞን 3 በተበታተነ መልኩ፣ የተቀሩት ኪስ ቦታዎቻቸው ላይ፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና በአብዛኛው፣ ምስራቅ ሐረርጌ በከፊል፣ ባሌ፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ሐረርጌ እና ምስራቅ ሸዋ በተበታተነ መልኩ እንዲሁም ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ ኪስ ቦታዎች ላይ፣ ከሶማሌ ክልል ጎዴ፣ አፍዴር፣ ቆራሄ፣ ሊበን፣ የዋርዴር ምዕራባዊ ክፍል እና የደገሃቡር ምዕራባዊ ክፍል በአብዛኛው፣ ፊቅ እና ጅግጅጋ በከፊል፣ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር በአብዛኛው፣ አኝዋክ በተበታተነ መልኩ፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ እና መተከል በአብዛኛው፣ ከማሺ በከፊል፣ ከትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን በከፊል፣ ሰሜን ምዕራባዊ ዞን በተበታተነ መልኩ፣ ምስራቃዊ እና ደቡባዊ ዞኖች ኪስ ቦታዎች ላይ እንዲሁም በሐረሪ ክልል እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በተበታተነ መልኩ እንደነበር ምሥሉ ያመለክታል። በሌላ በኩል የእፅዋት ሽፋኑ ከመደበኛ በታች (በፍራክሽን ከ -0.50 እስከ -0.03) የተስተዋለባቸው ከአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም እና ዋግህምራ በአብዛኛው፣ ሰሜን ወሎ እና ደቡብ ጎንደር በከፊል፣ የሰሜን ጎንደር ምስራቃዊ ክፍል፣ ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና አርጎባ ልዩ ወረዳ በተበታተነ መልኩ፣ በትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን በከፊል፣ መካከለኛው እና ምስራቃዊ ዞን በተበታተነ መልኩ፣ ከአፋር ክልል ዞን 5 በአብዛኛው፣ ዞን 4 በከፊል፣ የተቀሩት ዞኖች ላይ በተበታተነ መልኩ፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከማሺ ኪስ ቦታዎች ላይ፣ ከጋምቤላ ክልል መዠንገር በከፊል፣ አኝዋክ እና አሶሳ ኪስ ቦታዎች ላይ፣ ከሶማሌ ክልል ሽንሌ በተበታተነ መልኩ፣ ዋርዴር፣ አፍዴር፣ ሊበን፣ ጎዴ እና ደገሃቡር ኪስ ቦታዎች ላይ፣ ከኦሮሚያ ክልል ሆሮጉድሩ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ሸዋ፣ አርሲ፣ የባሌ ምዕራባዊ አጋማሽ እና ጉጂ በአብዛኛው፣ ሰሜን ሸዋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጅማ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ በከፊል፣ ምዕራብ ሐረርጌ እና ምስራቅ ሸዋ በተበታተነ መልኩ፣ የተቀሩት ኪስ ቦታዎቻቸው ላይ፣ ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የም ልዩ ዞን፣ ጌድዮ፣ ሲዳማ፣ ከፋ እና ጉራጌ በአብዛኛው፣ ኮንታ፣ የም፣ ደራሼ እና አማሮ ልዩ ዞኖች እንዲሁም ሀድያ፣ ጋሞጎፋ፣ ዳውሮ እና የቤንችማጂ ሰሜናዊ ክፍል በከፊል፣ ኮንሶ ልዩ ዞን፣ ደቡብ ኦሞ እና ወላይታ በተበታተነ መልኩ፣ የተቀሩት ኪስ ቦታዎቻቸው ላይ እንደነበር ምሥሉ ያመለክታል። የተቀረው ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ ጋምቤላ፣ ትግራይ፣ አፋር፣ እና ሐረሪ ክልሎች በአብዛኛው፣ አማራ እና ቤንሽንጉል ጉሙዝ በከፊል እንዲሁም ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ፣ ሶማሌ እና ኦሮሚያ በተበታተነ መልኩ መደበኛ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ እንደነበር እ.ኤ.አ የኖቬምበር 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት ከመደበኛዉ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ጋር ያለዉን ንፅፅር የሚያመለክተዉ ምስል ያሳያል (ካርታ 4 ይመልከቱ)።







| | |
|---|---|
| **ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 01 እስከ 10/2019 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን በሚሊ ሜትር** | **ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 01 እስከ 10/2019 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመቶኛዉ ጋር ሲነፃፀር** |